4127 Redwood Rd.
Oakland CA 94610
(510) 530-3681

No 2056/2018
Date 8-1-2018

**በሲያትል መካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ካቴድራል ሥርዓተ ቀብራቸው ለሚፈጸመው ለብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዜና ማርቆስ ከቅዱስ ሲኖዶስ የወጣ መግለጫ፤**

የሁላችን አባት የሆኑት ብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዜና ማርቆስ ድንገት ከመካከላችን በሞተ ሥጋ ተለይተው ባረፉበት ሰዓት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የብፁዕነታቸው ክቡር ሥጋ የሚያርፍበትን የመቃብር ቦታ ለማግኘት በልዩ ልዩ ሀገሮች ሙከራ አድርጎ ነበር። ቅዱስ ሲኖዶስ ያደረጋቸው ሙከራዎች እንደታሰበውና እንደተጠበቀው ሊሳካ ባለመቻሉና ሌላ አማራጭ በማጣቱ በቴክሳስ ክፍለ ሀገር በሂውስተን ከተማ በተመሠረተው የቅዱስ ሲኖዶስ ገዳም ክቡር ሥጋቸው በቋሚነት እንዲያርፍና ገዳሙም በብፁዕነታቸው ስም እንዲሠየም፥ለጊዜው ግን በሲያትል በጊዜያዊ ማረፊያ እንዲቆይ በወቅቱ የወሰነውን አፋጣኝ ውሳኔ እናስታውሳለን። በቴክሳስ በሚገኘው ገዳማችንም የመቃብሩን ፈቃድ ለማግኘት ብዙ ጥረናል። በጥረታችን መሠረት በልዩ ልዩ ምክንያት በፈለግነው ሰዓት ሊደርስልን አልቻለም። ይሁን እንጂ «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር» እንዳለ ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸምበት ሰዓት በደረሰ

ጊዜ ለረጅም ጊዜያት ከብፁዕ አቡነዜና ማርቆስ ጋር ባንድነት የኖሩት በሲያትል
መካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
ካቴድራል የሚገኙ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ባደረጉት ጥረት ብፁዕ ሊቀ ጳጳ
ስ አቡነ ዜና ማርቆስ በመሠረቱት፣ከብድርና ከእዳ ነጻ አድርገው ባሠሩትና በባ
ረኩት ከፍተኛ መንፈሳዊ አገልግሎትም ባበረከቱበት በሲያትል መካነ ብርሃን ቅ
ዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካቴድራል ክቡ
ር ሥጋቸው እንዲያርፍ ባደረጉት ጥረት መሠረት በልዑል እግዚአብሔር ፈቃ
ድ ጥረታቸው ተሳክቶላቸው ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ሕጋዊ ፈቃድ
ስላገኙ ሁላችንም እጅግ በጣም ተደስተናል።

የሲያትል መካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን ካቴድራልም የብፁዕነታቸው ክቡር አጽም አርፎበት የሚኖር
ስለሆነና ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ዋና ማዕከል ሆኖ ለዘላለም ስለሚኖር ይህ ደስ
ታ የቅዱስ ሲኖዶሱ ብቻ ሳይሆን ብፁዕነታቸውን የሚወዷቸውና የሚያከብሯቸ
ው የመላው ምእመናን ሁሉ ታላቅ ደስታ እና መንፈሳዊ ኩራት እንደሚሆን
በሙሉ ልባችን እናምናለን።

በዚህም መሠረት ነሐሴ 21 ቀን 2003 ዓ/ም ወይም ኦገስት 27, 2011
ለሚከናወነው ለብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዜና ማርቆስ የቀብር ሥነ ሥርዓት
ቅዱስ ሲኖዶስ ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል።

ስለዚህ የብፁዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዜና ማርቆስ የመንፈስ ቅዱስ ልጆች
የሆናችሁ ሁሉ ከላይ በተጠቀሰው ቀን በሲያትል መካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤ
ል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካቴድራል በመገኘት ለብፁዕ

ነታቸው የመጨረሻ አሸኛኘት እንድታደርጉ እየጠየቅን፥ በቴክሳስ ክፍለ ሀገር በሂውስተን ከተማ የሚገኘው በብፁዕነታቸው ስም የተሠየመው ገዳም መታሰቢያ ነቱ ለዘላለም በብፁዕነታቸው ስም እንደተሠየመ ሥራውም የሚቀጥል መሆኑን ም ልናሳስብ እንወዳለን።

የብፅዕነታቸው በረከት አይለየን።

አባ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ

የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ

